# ፕሮፌሰር ኃይሌ ላሬቦ

# በከፉ ቀን ለኢትዮጵያ ሕዝብ ገናና ታሪክ ጠበቃ ሆነው ሀቁን በማስረዳት ሸፍጠኞችንና ዘባቾችን እየተዋጉ ያሉ ጀግናና የታሪክ ሊቀ-ሊቃውንት

ከአስተዋይ በቀለ

ኢትዮጵያዊነትንና የማይገሰሰውን የኢትዮጵያ ገናና ታሪክ ተፃርረው በፕሮፌሰር ኃይሌ ላሬቦ ላይ የተነሱ አገር ከሃዲ ዘረኛ ቅጥረኛ ባንዳዎች ሁሉ ልብ ብለው ሊገነዘቡት የሚገባቸው ደረቅ ሃቅ፤ እናት ቅድስት አገር ኢትዮጵያችን የሠራዊት ጌታ የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን አገር መሆኗን ነው።

ስለሆነም፣ እያሱ ወልደ ነዌንና እስራኤልን ሊወጉ ግንባር ፈጥረው የተነሱ አሞራውያንን እግዚአብሔር ለእስራኤል ተዋግቶ ከከንዓን ምድረ-ገፅ እንዳጠፋቸው ሁሉ ፤ለኢትዮጵያም በኦሮሞ ሕዝብ ስም አገር ከድተውና ለጠላት ጥቅም ተሰልፈው ባልተገረዘ ምላሳቸው ፕሮፌሰር ኃይሌ ላሬቦን የሚሳደቡትንና የኢትዮጵያን ታሪክ የሚሸፍጡትንም ደምስሶ በማጥፋት እንደሚበቀልላት የታወቀ ነው።

ፕሮፌሰር ኃይሌ ላሬቦ ለታሪክ እውቀታቸውና ለኢትዮጵያ ሕልውና እንደ እሳት የሚፈትን መከራ ለመቀበል ፅኑ አቋም ያላቸው፣ ለዘረኞች መንጨርጨርና ለአገር ከሃዲዎች መፈራገጥ እጅ የማይሰጡ፣ ማንንም የማይፈሩ፣በራሳቸው፣በውቀታቸው፣በስራቸውና በአንደበታቸው ፍጽም ሙሉ እምነት ያላቸው ምርጥና እፁብ-ድንቅ ምሁር ናቸው።

በሰብዓዊ ባህሪያቸው ደግሞ፣ ለፈሪሃ እግዚአብሔር የተገዙ፣ከውስጥ ቅዱስ ከውጭ ጻድቅ የሆኑ፣ የተወደዱና የተከበሩ፣ቀናና ትሑት ሰው ናቸው።

መላ የኢትዮጵያ ሕዝብ እናት ትውለድ መንታ መንታውን እንደ ፕሮፌሰር ኃይሌ ላሬቦ ያለውን እያለ፤ በፕሮፌሰሩ ላይ የተሸረበውንና የተፈጸመውን ጥቃት ሁሉ በጥብቅ ያወግዛል።

## የኢትዮጵያ ታሪክ ለዘላለም ገናናና የማይገሰስ ነው ! ! !

## የተሟላ ጤንነትና ረጂም እድሜ ለፕሮፌሰር ኃይሌ ላሬቦ ! !